# ፍትሃዊ፣ ተገቢና ተመጣጣኝ እርምጃ

## ክፍል አንድ

*አዲስ ቶልቻ 08/17/13*

1434ኛው የኢድ አልፈጥር በአል ባለፈው ሳምንት ነሀሴ 2፣ 2005 ዓ/ም በመላው ዓለም ሙስሊሞች ዘንድ በድምቀት ተከብሮ ውሏል። በኢትዮጵያም በተመሳሳይ በሁሉም ክልሎች በአዲስ አበባም  በድምቀት ተከብሯል። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ አበባ ስታዲየም በኢድ የፀሎት ስነስርዓት ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊም የከተማዋ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።

ይሁን እንጂ በተለይ በአዲስ አበባ በተከበረው የኢድ አልፈጥር በአል ላይ በጠቅላላ በፀሎት ስነ ስርዓቱ ላይ ከተገኙት ሙስሊሞች ጋር ሲነፃፀሩ እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ከሃይማኖታዊ ስርዓቱ ውጭ የሆኑ አጀንዳዎችን አንስተው ሁከት ለመቀስቀስ ሞክረዋል።

እነዚህ በጥቂት ሺሆች የሚቆጠሩ የኢድ የፀሎት ስርዓቱን ሊያውኩ የሞከሩ ወጣቶች፣ ለሰላማዊ ሙስሊሞችና ለተቀረውም ህዝብ አዲስ አይደሉም። ከአንድ አመት በላይ በመጀመሪያ በአወሊያ መስጊድ፣ በኋላም በአንዋር መስጊድ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ እዚያው አቅርቢያ በሚገኘው በኒ መስጊድ በርካታ ሙስሊሞች የሚታደሙበትን ሳምንታዊ የአርብ የፀሎት ስርአት ሲያውኩ መክረማቸው ይታወቃል። ህዝብን ለተቃውሞ እንዲወጣ ማድረግ የሚያስችል አጀንዳ ያጣው ሰማያዊ የተሰኘው ፓርቲም የአወሊያና የበኒ መስጊድ የአርብ አዋኪዎቹን የሚከረከር አጀንዳ አንስቶ በአደባባይ አንጫጭቷቸዋል።

የኢድ በአል ከመድረሱ ከአንድ ሳምንት በፊት በመጨረሻው የረመዳን ወር ፆም የአርብ የፀሎት ስነስርዓትን እናውካለን የሚል አዋጅ መለፈፋቸውን ተከትሎ የፌዴራል ፖሊስ ባወጣው ማሳሰቢያ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸው እንደነበር ይታወሳል። የፌዴራል ፖሊስ በሰጠው ማስጠንቀቂያ የኢፌዴሪ ሕገመንግስት በሃይማኖትና በፖለቲካ መሃከል ግልፅ ልዩነት ማስቀመጡን አስታውሶ፣ “ሃይማኖቶችን ከፖለቲካ ተፅእኖ ለመጠበቅም ማናቸውም አይነት በህግ ፍቃድ የተሰጣቸው የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሰልፎችና ህዝባዊ ስብሰባዎች በፀሎትና በአምልኮ ቦታዎች ሃይማኖታዊ አገልገሎት ላይ እንዳችም ጫናና ተፅእኖ ማድረግ በማይቻልበት ርቀት እንዲካሄዱ በሕግ እንዲወሰን መደረጉ ይታወቃል።”ይላል።

ይህም በማናቸውም ሃይማኖታዊ ስርዓት በሚከወንባቸው አካባቢዎች፣ ለሃይማኖታዊ ስርዓት የታደመው ህዝብ ላይ ጫና ለማሳደር ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ህዝባዊ ስብሰባ በአካባቢው ማካሄድ የተከለከለ መሆኑን በግልፅ ያመለክታል። ከልከላው ያልተፈቀዱ ህገወጥ ሰላማዊ ሰልፎችንና ህዝባዊ ስብሰባዎችን ብቻ ሳይሆን የተፈቀዱትንም የሚያጠቃልል ነው።

እንግዲህ ከአንድ ዓመት በላይ በአርብ የፀሎት ስርዓት ላይ ስውር የፖለቲካ አጀንዳ ባላቸው ቡድኖች የሚመሩ ጥቂት ስሜታዊ ወጣቶች ሲያካሂዱት የነበረው ሁከት ህገወጥ ነበር። ከዚህ ሁከት ጋር በተያያዘ ብዙዎች "መንግስት አንድ አመት ሙሉ  በቸልታ ተመለከተ" የሚል ቅሬታ ሲያቀርቡ አድምጠናል። እርግጥ፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ከዚህ ቀደም ሲያሳየው ከነበረው ታጋሽነት የተለየ አይደለም ያሉም አሉ።

ያም ሆነ ይህ የፖሊስ ማሳሰቢያ መውጣቱን ተከትሎ በማግስቱ የተካሄደው የአርብ የፀሎት ስርዓት በሰላም ተከናውኗል ። በዚህ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሙስሊሞች እፎይታ እንደተሰማቸው ገልፀዋል። በቀጣይነት በፀሎት ስፍራ ሰላማዊና የተረጋጋ ሁኔታ ለመፍጠር ከፖሊስ ጋር በመተባበረ እንደሚሰሩም ቃል ገብተው ነበር።

የፖሊስ ማሳሰቢያ በወጣ በሳምንቱ በተካሔደው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በተገኙበት የኢድ ፀሎት ላይ ድምጻችን ይሰማ በተሰኘው ከሃይማኖታዊነት ይልቅ ፖለቲካዊ አካሄዱ ጎልቶ የሚታየው፣ እንዳመቺነቱ ከግንቦት ሰባት ጋር፣ ሌላ ግዜ ደግሞ ሕጋዊና ሕገወጥ አካሄድን እያጣረሱ ከሚከተሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓረቲዎች ጋር፣ እንዲሁም ከግብጹ ሙስሊም ብራዘርሁድ ጋር በሚንቀሳቀሰው "ድምጻችን ይሰማ" ተተሰኘ ቡድን የሚጋልባቸው ስሜታዊ ወጣቶቹ ሁከት ለመቀስቀስ ሞክረዋል።

በሁሉም የአዲስ አበባ መስጊዶች የሚሰግዱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በአንድ በታደሙት በዚህ የኢድ ፀሎት ላይ ለመቀስቀስ የተሞከረው ሁከት በግልፅ ያሳየን ነገር አለ። ይህም አዋኪዎቹ ከጠቅላላ የአዲስ አበባ ሙስሊሞች ጋር ሲነፃፀሩ እፍኝ የማይሞሉ መሆናቸውን ነው። ብዙ የሚመስሉት ስለሚጮሁ ብቻ መሆኑን ታዝበናል። እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሙስሊም ክቡሩን የፀሎት ስርአት እያወኩ ሲያሸማቅቁት ስለቆዩ አንደሚፀየፋቸውም መገንዘብ ችለናል፡፡

በኢድ ፀሎት ስርአት ላይ ሁከት ለመቀስቀስ የተደረገውን ሙከራ ተከትሎ፣ የዚህ አይነት የፖለቲካ አጀንዳ ላይ የተመሰረተ አቋምን ሃይማኖታዊ ስርአት በሚፈፀምበት ቦታ በምዕመናን ላይ ጫና ለማሳደር በማንፀባረቅ ረብሻ መፍጠር ህገወጥ ድርጊት ስለሆነ፣ የዚህ ድርጊት ፈፃሚዎች ምናልባት

ግንዛቤ የላቸውም ይሆናል በሚል ግምት ፖሊስ ማሳሰቢያ የሰጠ በመሆኑ፣ አድመኞቹ ከሁከቱ እንዲታቀቡ እርምጃ ወስዷል። ይህ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ሙስሊም ምዕመናንን ሰላም ለማረጋገጥና አዋኪዎቹን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ የተወሰደው እርምጃ ተገቢና ህጋዊ ነው። ሰላም ወዳድ ሙስሊሞችና የተቀረው ህብረተሰብም እርምጃው በመወሰዱ የተሰማውን አዎንታዊ ስሜት ገልጿል። መንግስት በቀጣይነትም ህጋዊ እርምጃ በመውሰዱ መቀጠል እንደሚገባውም አሳስቧል።

ሰላማዊ ሙስሊሞችና የተቀረው ህበረተሰብ የኢድ የፀሎት ስርአቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ ህጋዊና ይበል የሚያሰኝ ነው ቢሉም፤ አዋኪዎቹ በህገወጥ አካሄድ መንግስት ላይ ጫና ያሳድራሉ፣ ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ሊመጣ የሚችልበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ ብለው ተስፋ አድርገው የነበሩ አንዳንድ አካላት ግን ቅሬታ እንደተሰማቸው አልሸሸጉም። ከእነዚህ መሃከል የተወሰኑት በተገቢና ሕጋዊ እርምጃ ላይ የተሰማቸውን ቅሬታ በአግባ  አድበስብሰው ሲገልፁ የተቀሩት ግን - ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱትም ሕገወጦቹም ተቃዋሚዎች  በእርምጃው ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በይፋዊ መግለጫ አሳውቀዋል።

ከእነዚህ መሃከል በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት የተፈረጀውና የኤርትራን ኢትዮጵያን የማተራመስ አላማ ለማስፈፀም ገንዘብ እየተከፈለው የሚዳክረው ግንቦት 7 ቀዳሚው ነው፡፡ ሌላው ሕገወጥ መግለጫ አውጭ በግል ችግራቸው በኢትዮጵያ ያለውን መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው ያፈሩትን ሃብት በትነው ወደ ውጭ አገር ኰብልለው በፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የታግገቱትና  በተቃዋሚነት እንዲሰለፉ የተገደዱት የዩኒቲ ዩኒቨርስቲ መስራችና ባለቤት የነበሩት ዶ/ር ፍሰሃ እሸቴ አደራጀሁት የሚሉት በተግባር ግን ራሳቸውን ብቻ በአባልነት የያዘው “የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት” የተሰኘ ምንነቱ የማይታወቅ አካል ነው።

ሕጋዊ ሆነው በአገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት መሃከል ደግሞ፣  የኢድ አልፈጥር በአል ላይ ሁከት ለመቀስቀስ ሞክሮ የነበረውን ቡድን “ሰልፌን እምቅልኝ” ብሎ ጠርቶ ደጋፊ ያለው መስሎ የቀረበው ሰማያዊ ፓርቲ ቀዳሚው ነው፡፡ ሰልፉን ስላሞቁለት ውለታ ለመመለስ ያደረገው ነው፡፡ ለወደፊት ሌላ ሰልፍ ቢጠራ ከጎኑ የሚቆሙት እነዚሁ አዋኪ ጎረምሶች ስለሆኑ ወዳጅነቱን ለማጽናትም ነው፡፡

ሌላው መግለጫ አውጪ ሕጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓረቲ ነው፡፡ አንድነት መግለፃውን ተንሰፍስፎ ያወጣው እውነት መግለጫ የሚያስፈልገው ጉዳይ ተፈጥሮ ሳይሆን፣ ሰሞኑን “የፀረሽብርተኝነት ሕጉን አስሽራለሁ” ብሎ ለተነሳበት ተገቢ ያልሆነ

ዘመቻ የጸረሽብርተኝነት ሕጉ አላላውስ ያላቸውን አክራሪ እምቅ አሸባሪዎች ከጎኔ ይሰለፋሉ ብሎ ተስፋ ስላደረገ ነው፡፡ ሰልፍ ለማሞቅም ያስፈልጉታል፡፡

ስወር የፖለቲካ አጀንዳ ያለው የእስልምና ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገው እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በሚያስተዛዝብ አኳኋን ጉዳዩን ሲያጋግል የቆየው የአሜሪካ ድምፅ የአማርኛ ፕሮግራምም አርምጃውን በይፋ ባይቃወምም፣ ጋዜጠኞቹ በጉዳዩ ላይ ባቀረቡት ዘገባ ለሁከቱ ያላቸውን ድጋፍ የሚያሳይ ስሜታቸውን አንጸባርቀዋል። ይህም ሃሙሰ ነሀሴ 2፣ 2005 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ ባሰራጨው ዘገባው "1434ኛ የኢድ አልፈጥር  በዓል ዛሬ በአዲስ አበባ ሲከበር ብዙሃን ሙስሊም ምዕመናን ተቃውሚቸውን ገልፀዋል።" ሲል አስተላልፏል።

የቪኦኤ ጋዜጠኞች በአዲስ አበባ ኮሮስፖዳንት ስላላቸወ በዕለቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በታደሙበት የኢድ አልፈጥር ልዩ የፀሎት ስርአት ላይ ህገወጥ ተቃውሞ ሊቀሰቅሱ የሞከሩት እጅግ በጣም ጥቂት፣ በተጋነነ ግምት ከ10 ሺህ የማይበልጡ መሆናቸውን ያውቁታል። የቪኦኤ የአማረኛ ፕሮግራም ጋዜጠኞች በየሳምንቱ አርብ "ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን መንግስትን ተቃወሙ፣ ተንገላቱ፣ ተፈለጡ፣ ተቆረጡ . . ." እያሉ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሲዘግቡ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ የሚያቀርቡዋቸው ዘገባዎች መንግስት በሙስሊሙ ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት  የሚያስመስሉ ነበሩ፡፡

እንዲሁም  ሁሉም በአንዋርና በኒ መስጊዶች ለጸሎት የወጡ ሙስሊሞች በተቃውሞዎቹ ላይ የተሳተፉ ለማሰመሰል ይጥሩ ነበር፡፡ በሰሞኑ የኢድ አል ፈጥር የፀሎት ስርአት ላይ ጁመአን ከመቶ በላይ በሚሆኑ የአዲስ አበባ መስጊዶች ይሰግዱ የነበሩ ሁሉም የአዲስ አበባ  ሙስሊሞች በአንድ ላይ ሲታደሙ፣ አዋኪዎቹ እፍኝ የማይሞሉ  መሆኑ ሲጋለጥ ለሁከቱ ያላቸውን ድጋፍና አይዞህ ባይነት ለመግለጽ ነው በውሸት "ብዙሃን ሙስሊም ምእመናን ተቃውሚቸውን ገለጹ" የዘገቡት።

የቪኦኤ ጋዜጠኞች እኔ እስክሚገባኝ ድረስ ደሞዝ  የሚከፍላቸምንና የሬዲዮ ጣቢያው ባለቤት የሆነው የአሜሪካ መንግስት ኢትዮጵያን በተመለከተ ከሚያራምዳቸው አቋሞች በተቃራኒ የአክራሪዎችን ሕገወጥ የመንግስት ተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን የመደገፍ አዝማሚያ ሲያንጸባርቁ ነው የቆዩት፡፡  ዕውን ቢሆን ለአገሪቱ ዘላቂ ሕልውና አደገኛ የሆነውን፣ ከዚህም አልፎ አገሪቱን የዓለም አቀፍ አሸባሪዎች መጠለያ በማድረግ ዳፋው ለሌሎችም የሚተርፈውን የአክራሪነት እንቅስቃሴ በዘገባዎቻቸው ከመደገፍ ባሻገር ለአዋኪው ቡድን የህዝብ ግንኙነት ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

በዚህጉዳይ ላይ የቪኦኤ የአማርኛ ፕሮግራም ላይ የሚሰሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች የያዙት አቋም ከአሜሪካ መንግስትና በአጠቃላይ ከምእራባውያን  አቋም ያፈነገጠ መሆኑን ለማሳየት ላለፉት ሶስት አመታት በኢትዮጲያ የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው ያገለገሉት ተሰናባቹ አምሳደር ዶናልድ ቡዝ ሰሞኑን የተናገሩትን ልጥቀስ፡፡

አምባሳደር ዶናልድ ቡዝ ለኢትዮጵያ የግል መገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ "ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች አገር ነች፡፡ ይህ ስብጥር እንደረጋ እንዲቆይ የአገሪቱ ሕገመንግስት የእምነት ነጻነትና እኩልነትን አረጋግጧል፡፡ በሕገመንግስቱ ሃይማኖቶች በመንግስት ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ፣ ብሕገመንግስቱ መቀመጡ መሰረታዊ ነው፡፡ ይህ መሆኑ የትኛውም ሃይማኖት ነጻነት እንዲኖረውና ለተከታዮቹም የመረጡትን ሃይማኖት የመከተል መብት ይሰጣል፡፡ አሁን ካለው ሁኔታ የምንረዳው ግን አንዳንድ ሰዎች ይህን የመቀየርና የራሳቸውን እምነት በሌሎች ላይ በግድ የመጫን ፍላጎትና አመለካከት መኖሩን ነው፡፡" ብለዋል፡፡ ታዲያ ይህ ከቪኦኤ ጋዜጠኞች ለአክራሪዎች እንቅስቃሴ ከሚያሳዩት ተቆርቋሪነትና አይዞህ ባይነት ጋር አይቃረንም?

ሕጋዊ ሁነው በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትና በውጭ የተሸሸጉት ሕገወጦቹ ተቃዋሚዎች የፀሎት ስርአት በሚረብሹ  አዋኪዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ ተቃውመው ወዳወጡት መግለጫ ልመለስ፡፡ ሕገወጡ ግንቦት 7 ኢትዮጵያ ጳግም አገር መሆን በማትችልበት ሁኔታ ለማተራመስ ያለመው የኤርትራ መንግስት አቋም አስፈጻሚ ቅጥረኛ በመሆኑ ለኢትዮጵያ አደጋ የሆነ ማንኛውንም እንቅስቃሴና አቋም የመደግፍ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ግንብት 7 የአክራሪዎቹን እንቅስቃሴ የደገፈው በአዋኪዎቹ ላይ የተወሰደውን እርምጃም የተቃወመው ከዚህ ዓላማው በመነሳት ነው፡፡ የግንቦት 7 አቋም ያስገርም የነበረው ፖሊስ ሁከት የቀሰቀሱ የአክራሪ ጀሌዎች ላይ የወሰደውን ሕግ የማስከበር እርምጃ ደግፎ ቢሆን ነበር፡፡ በመሆኑም የኤርትራ ተላላኪውና ምንደኛው ግነቦት 7 ያወጣው መግለጫ ላይ ዝርዝር  ጉዳዮችን ማንሳት አስፈላጊ አይደለም፡፡

ታጋቹ ፖለቲከኛ ዶ/ር ፍሰሃ እሸቴ ራሳቸውን "ምክር ቤት" ብለው ሰይመው ያወጡት መግለጫም ሰውየው ትክክለኛ የሆነ አቋም የመያዝና የመግለጽ መብትና ነጻነታቸውን ተቀምተው ግንቦት 7ን የመሳሰሉ የአጋቾቻቸውን ቡድኖች አቋም ከማንጸባረቅ ውጭ አማራጭ ስለሌላቸው የቀባጠሩትን እንደራሳቸው አቀም አድርጎ መተቸት ተገቢም አስፈላጊም አይደለም፡፡

አሁን ሕጋዊ ተቃዋሚዎች ነን በሚል አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ - አንድነትና ሰማያዊ ፓርቲ የባለፈው ኢድ የጸሎት ስርአት አዋኪዎች ላይ ፖሊስ የወሰደውን እርምጃ ተቃውመው ያወጡዋቸውን መግለጫዎች እንመልከት፡፡

አንድነት ያወጣው መግለጫ “ ሙስሊም ወገኖቻችንን መግደል፣ ማሰርና መደብደብ ሕገወጥነት እንጂ መፍትሄ አይደለም” የሚል ርዕስ አለው፡፡ አንድነት ለመግለጫው የሰጠው ይህ ርዕስ ራሱ ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡ ይህም ሕገወጥ ያለውን እርምጃ ተመልሶ መፍትሄ አይደለም ማለቱ ነው፡፡

አንድነት “እርምጃው መፍትሄ አይደለም” ካለ፣ አንድ መፍትሄ የሚሻ ችግር መኖሩን መቀበሉን ያመለክታክል፡፡ አንድነት በይፋ ሲናገር እንደሰማነው ግን እስልምናን ሽፋን ያደረገ የአክራሪነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መኖሩን አይቀበልም፡፡ አክራሪነትን እንደችግር ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ፣ “ እርምጃው መፍትሄ አይደለም” ሲል መወሰድ ያለበት አማራጭ እርምጃ አለ ማለቱን ያመለክት ነበር፡፡ ግልጽነት የጎደለው ነው ያልኩት ለዚህ ነው፡፡ እርግጥ እንደሌሊት ወፏ ወፎችን ስታገኝ “እዩኝ እንደናንተ ክንፍ አለኝ፣ እንደናንተ እበራለሁ ወገናችሁ ነኝ፣” አይጦችን ስታገኝ ደግሞ “እዩኝ እንደናንተ ጡት አለኝ አጠባለሁ ወገናችሁ ነኝ” እያለች እየተልመጠመጠች በሀለት ቢላዋ ስትበላ እንደነበረችው ወፍ መሆን አሰኝቶትም ሊሆን ይችላል፡፡ አክራሪዎቹንም የኢትዮጵያን ሕዝብም እንዳያጣ ሁለቱንም መስሎ ለመታየት፡፡

አንድነት እየተልመጠመጠ ያንንም ይህንንም መስሎ ለማደር የሚደረግ ሙከራ የተጋለጡ ቀን ሁለቱንም እንደሚያሳጣ ዘንግቶታል፡፡ የሚያዋጣው በይፋ ከሕዝብ ወይም ከአክራሪዎቹ ወገን መሰለፍ ነው፡፡ ይህ ተልመጥማጭነቱ ፓርቲው አቋም ይዞ አገር ለመምራት የሚያስችል ጥንካሬ የሌለው መሆኑንም ያመለክታል፡፡

ወደዋናው የአንድነት መግለጫ ይዘት ስመለስ አንድ ገጽ ያህል የሚሆነው መግለጫ ላይ የሰፈረው ሃሳብ ሲጠቃለል “ ለሰላማዊ የሙስሊሞች የመብት ጥያቄ መንግስት የሃይል እርምጃ ወስዷል” የሚል ይሆናል፡፡

አንድነት ሁለት አመት ሞላው ያለውን ጉዳይ “ሰላማዊ የሙስለሞች የመብት ጥያቄ” ብሎታል፡፡ መንግስት “ይህን የመብት ጥያቄ እንዲያከብር፣ በዕምነት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን አቁሞ ወደ ውይይት በመምጣት ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ምላሽ እንዲሰጥ አሳስቤያለሁ” ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይፋ የቀረበው በ2004 ዓ/ም አጋማሽ ላይ በአዲስ አበባ አወሊያ መስጊድ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ተጠራርተው እርስ በርስ በመመራረጥ በተቋቋመ ቡድን አማካኝነት እንደነበረ ይታወሳል፡፡ ይህ ቡድን መላውን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚወክል ሳይሆን በአወሊያ ተቋም አካባቢ ውስጥ ውስጡን ተጸንሶ የነበረው የዋሃቢ ሰለፊ የአክራሪነት አመለካከት አራማጅ ቡድን ነው፡፡ የቡድኑን እንቅስቃሴ በቅርበት የሚያውቁ እዚያው አካባቢ የነበሩ ሰዎች በይፋ በሰጡት ምስክርነት አንድ ሺህ አምስት መቶ ያህል ሰዎች ተሰብስበው የመረጡዋቸው እንኳን የኢትዮጵያ ሙስሊም ማሕበረሰብ አንድ ቀበሌንም የማይወክሉ ናቸው፡፡

ጥያቄውን አነሱ የተባሉት አስራሰባት ገለሰቦች በዚህ አኳኋን ጥቂት ሰዎች የመረጡዋቸው ቢሆኑም፣ መንግስት በሕገመንግስቱ መሰረት ማንኛውም ዜጋ ተበድያለሁ ብሎ ሲያስብ አቤቱታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን ታሳቢ በማድረግ አቤቱታቸውን ተቀብሎ ለችግሩ ሰላማዊ እልባት ላበጀት አወያይቷቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰዎች የወከሉዋቸው አስራሰባት ግለሰቦች አቤቱታቸውን አቀረበዋል፡፡

ካቀረቡዋቸው አቤቱታዎች፣ "የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ሃላፊነታቸውን የማስረከቢያ ግዜያቸው ስላለፈ የምክር ቤቱ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ፣ አወሊያ የተሰኘው የራሱ መስጊድ ያለው እስላማዊ ተቋም ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ እንዲመለስ፣ አሕባሽ የተሰኘ አስተምህሮ በግዳጅ እየተሰጠ ስለሆነ ይህ እንዲቆም ይደረግ" የሚሉት አውራዎቹ ነበሩ፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አካላት በተደጋጋሚ ማብራሪያ የሰጡበት ቢሆንም አሁንም ተያያዥ ጉዳዮች ስለተነሱ ወደኋላ ተመልሶ መመልከትን አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ ለጥያቄዎቹ የተሰጠውን ምላሽ በክፍል ሁለት ጽሁፍ እመለስበታለሁ፡፡